# አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ፤ እሰየው እንኳን ደስ ያለህ

## ጌታቸው ኃይሌ

"የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ ፤ ማሰቃያ እስር ቤቶች ይዘጋሉ" ብለህ ማወጅህ የሕዝብን ዋይታ መስማትህን ያመለክታል ። "ደስ አለኝ" ልትል የሚገባህ አሁን ነው ፤ እኛም "አሜን ፥ ይገባሃል ፤ እንኳን ደስ ያለህ" እንላለን ። ቃልክን ከጠበቅህ በሰው ፊት ኰርተህ መራመድ ትችላለህ ።

ዜናውን እንዳሰራጫችሁት ብዙ ተተችታችኋል ። "እንደለመዱት ሊደልሉን ነው ፤ ቃላቸውን ሲጠብቁ አይተናቸው አናውቅም" የሚሉ ሰዎች ቍጥር ጥቂት አይደለም ። "ያሁኑ እርግጠኛ ነው" እንዳልል የምረታበት ማስረጃ የለኝም ። የሚያዋጣው ቃላችሁን ስትጠብቁ ማየት ነው ። "የማእከላዊን ስም እንለውጠዋለን" ያልከው ማፈግፈግህ እንዳይሆን ተጠንቀቅ ። መለስ ዜናዊ ስሙ ቢለወጥ ዴሞክራት ይሆን ነበር እንደማለት ነው ።

ሕዝባችን በአስተዳደራችሁ የደረሰበትን ሥቃይ ብዙዎች ዘርዝረውታል ። ዝርዝሩ ቀለም ከማለቁ በፊት ስለማያልቅ አሁን ወደዚያ አልሄድም ። "ዱሮውንም እዚህ ባልደረስን ነበር" ማለትም ጥቅም የለውም ፤ ደርሰናል ። "ለምን እንዲህ ሆነ?" ማለት የፈሰሰ ወተትን አፍሶ ለመጠጣት መሞከር ይሆንብናል ። የታሪክን ሂደት መቆጣጠር የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው ። አዋጃችሁ አንዱን እየሄዳችሁበት ሳለ ፥ መቈጣጠር እንደሚቻል ካያችሁበት ቅጽበት የደረሳችሁ አስመስሎታል ፤ ግፉበት ። የፀሐይ ጮራ አይተናል ። ፀሐይ መውጣት ከጀመረች ሐሳቧን አትቀይርም ። ትወጣለች ። ታሪክ እንደነገረን ሐሳቧን ከቀየረች የምትቀይረው አንዳች የተጀመረ በጎ ሥራ ሳያልቅ አልጠልቅም ብላ ጨለማን ለመግታት ብቻ ነው ።

አንድ ጊዜ አንድ ንጉሥ ፥ "የጊዜው ሁኔታ እንዴት ነው?" ብሎ ፈላስፎችን ቢጠይቅ ፥ "ጊዜ እኮ አንተ ነህ ፤ ጥሩ ካደረከው ጥሩ ይሆናል ፤ ካበላሸኸው ይበላሻል" ብለው መለሱለት ። ይኸ የሆነው ንጉሥ ፈላጭ ቈራጭ በነበረበት ዘመን ነው ። ኢትዮጵያን የምታህል አገር ፈላጭ ቈራጭ በተወገዘበት ዘመን እጃችሁ ላይ ወድቃለች ። ልታውቧት ፥ ልታተልቋት ስትችሉ ፥ ለምን ትኰስምን? ለምን ትነስ? ፖለቲካ ለፈላጭ ቈራጭ ፖለቲከኞች ወይ የመቃብር መቆፈሪያ ወይም የሐውልት ማቆሚያ ስፍራ ነው ። የመረጣችሁትን ልታደርጉት ትችላላችሁ ። አያድርስና ፥ በጭቆናው ከቀጠላችሁበት መቃብራችሁን መቈፈራችሁ ፥ ሕዝብ ሲያልም የኖረውን የሞተለትንም ዲሞክራሲ ካስገኛችሁ ደግሞ ሐውልታችሁን ማቆማችሁ ነው ። ቀባሪውም ሆነ ሐውልት አቋሚው ሥራችሁን የሚመዘግብ ታሪክ ነው ። ዓለም የሚያስታውሳቸውን ፖለቲከኞች ልብ በሏቸው ። ፖለቲከኛ ሆኖ የአንድን ሕዝብ ሕልም ከማድረስ የበለጠ ምን ደስታ አለ?

መጨቄን የሚያስደስተው ሰው የለም ማለቴ አይደለም ። ግን እስከሁን ያ ሰው መሆናችሁን በእውነት ታውቁታላችሁ? እንዴት ብሎ!! መግዛት ለመደነቅ ነው ፤ ለመረገም አታድርጉት ።

“የምንሠራው የሕዝብን ብሶት ለማስወገድ ነው” የምትሉ ከሆነ ፥ የራሳችሁን ስሜትና የሕፃናት ለቅሶ ብቻ አዳምጣችሁ መሆን አለበት ። የብዙኃኑ ብሶትስ? ለዚያውም ያመጣችሁት መፍትሔ አዲስ ብሶት ፈጠረ እንጂ አንዳችም ብሶት አልፈታም ። መፍትሔያችሁ እስካሁን ለሰማችሁት ፥ ልትሰሙም ለፈለጋችሁት ችግር ነው ፤ እሱውም ፥ “አንዱ የኢትዮጵያ ነገድ (እናንተ “ብሔር” የምትሉት) ሌሎቹን ነገዶች ጨቁኗል” የሚባለው ብሶት ነው ። ይኸ ብሶት የብዙኃኑ ሳይሆን የናንተና የመሰሎቻችሁ ነው ።

በሁላችንም ላይ የጫናችሁት የብሶታችሁ መፍትሔ “ተለያዩ” የሚል የናንተን ፍላጎት የሚያረካ ነው ። ብዙኃኑ ሕዝብ እምቢ እያለ ፥ ለያይታችሁን አገሪቷን ወደ ዜጎቿ መታጐሪያ ክልል ለወጣችኋት ። ክልልና የጻፋችሁት ሕገ መንግሥት አገሪቷን United Nations አደረጓት ። ከዚያም አልፈው የእስር ቤት ታላላቅ ወንድሞች ስለሆኑ ፥ ከማሠቃያ እስር ቤቶች ጋር አብራችሁ አፍርሷቸው ። ሕዝቡ የሚለው ፥ “በገዛ አገራችን የቁም እስረኞች አታድርጉን ፥ በዲሞክራሲ አስተዳደር እንድንኖር ልቀቁን” ነው ። እምቢ እያላችሁ ፥ “እንሻሻላለን” እያላችሁ ሕዝቡ የጠየቀውን በናንተ ጥያቄ አትለውጡት ። ሕዝቡ ልቀቁን እንጂ ተሻሻሉልን አላለም ።

ሕዝቡ የሚጠይቀው በዲሞክራሲ አስተዳደር ዕለታዊ ችግሩን እያስወገደ በነፃነት መኖር ነው ። እናንተ ግን “የሰጠንህ አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ ነው” ትላላችሁ ። የዲሞክራሲ አስተዳደር ሕዝቡ የሚቀርጸው ነው እንጂ ማንም የሚሰጠው አይደለም ። የዲሞክራሲን አስተዳደር መስጠት የዲሞክራሲን አስተዳደር መንፈግ ነው ። ሕዝቡ የሚጠይቀው “አንድ የሆንነውን ኢትዮጵያውያን የማይመስል ምክንያት እየፈለጋችሁ አትከፋፍሉን” ነው ። ሕዝቡ ፥ “የነገድ መለዮ ያደረጋችሁት ካርድ ዱሮውንም መኖር የለበትም” እያለ ሲጥለው ለምን ትቆታላችሁ? የገዢ ኩራቱ ሕዝብን አንድ ማድረግ እንጂ ፥ መከፋፈልና የተፋቀሩትን ማጣላት እኮ የሰይጣን ሥራ ነው ።

እናንተ እንደምታስቡት ፥ የቋንቋ ብዛት የተለያዩ ሕዝቦች እንደማያደርገን ዐዋቂዎች ሲነግሯችሁ አልሰማ ማለታችሁ ለምንድነው? “ስለዚህ ጉዳይ ከዐዋቂዎቹ የበለጠ ዕውቀት አለን” ብላችሁ ነው ወይስ ሰዉ እንደሚያማችሁ ፥ “ዐዋቂዎችን ከሰማን ከፋፍሎ መግዛት ይቀርብናል” ብላችሁ ነው? ይኼ ሐሜት ሳይሆን እውነተኛ ነገር መሆን አለበት ። ሐሜት ባይሆንማ ፥ አማራዎችና ኦሮሞዎች (በአንድ ወቅት “አልፋና ኦሜጋ” አንድ እንዲሆኑ ሐሳብ ያቀረብኩላቸው) “አንድ ነን” ሲሉ አትቆጡም ነበር ። ቋንቋ እንደልብስ ነው ፤ ኢትዮጵያዊ ልብስ የለበሰ ፈረንጅ ሁሉ ኢትዮጵያዊ አይሆንም ፤ በዚያው አንጻር የፈረንጅ ልብስ የምንለብስ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፈረንጆች አይደለንም ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሴማዊና ኩሻዊ የሚባሉ ቋንቋዎች አሉ ። ተናጋሪዎቻቸው ግን ሁሉም ኩሻያን/ኢትዮጵያውያን ናቸው ።

የሕዝብን ብሶት መስማቱን ቀጥሉበት ። በሚገኘው ድል ተጠቃሚዎቹ እናንተን ጨምሮ ሁላችንም ነን ። ካወቅንበት ኢትዮጵያ እኛን አበልጽጋ ሌሎችን የምታበለጽግ ፥ እኛን አቅፋ ሌሎችን የምታስጠጋ ሰፊና ሀብታም አገር ናት ።

የኢትዮጵያ አምላክ የጀመራችሁትን አዲስ ጉዞ ከፍጻሜ አድርሶ ከጨቋኝነት ነፃ ያውጣችሁ ።